# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ

## የተማሪዎች የሥነ-ምግባር መመሪያ

ታህሣሥ 2017 ዓ.ም

ወራቤ

**መግቢያ**

በርካታ ተመራማሪዎች እንደሚስማሙት መማር ማለት የባህሪይ ለውጥ ማምጣት ማለት ነው፡፡ ትምህርት ደግሞ ለመማር አዳዲስ ነገሮችን ከሌሎች የምንቀበልበትና ያለንን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለሌሎች የምናካፍልበት ወይም የምንሰጥበት ሂደት ነው፡፡ በትምህርት አማካይነት ዜጎች በዕውቀት፣ በአስተሳሰብ፣ በግንዛቤ፣ በችሎታና በክህሎት ዳብረው እና በሥነ-ምግባር ታንጸው ለአጠቃላይ ማህበራዊ ዕድገት ንቁ ተሣታፊ መሆን እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

በዚሁ መሠረት በሥነ-ምግባራቸው ምስጉን፣ አገር ወዳድና ኃላፊነት የሚሰማቸው፣ የዲሞክራሲ አስተሳሰብን የተላበሱ ተማሪዎችን ለማፍራት የሚደረገውን ጥረት ለማገዝና የሥነ-ምግባር ግድፈት የሚታይባቸውን ለማስተማርና ለማረም እንዲረዳ የሥነ-ምግባር መመሪያ በሁሉም የመንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑና የግል የትምህርት ተቋማት ላይ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 15 ለክልሉ ትምህርት ቢሮ በተሠጠው ስልጣን መሰረት ይህ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የተማሪዎች ሥነ-ምግባር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ ሁኔታ

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ “በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ትምህርት ቢሮ የተማሪዎች የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር ……./2017” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2. ዓላማ**

ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ በመፍጠር፣ ተማሪዎችን በመልካም ሥነ-ምግባር በማነጽ፣ የተማሪዎችን መብትና ደህንነት በማስከበር እና ብቁ ዜጎች እንዲሆኑ በማስቻል የተማሪዎችን ውጤትና ሥነ-ምግባር ለማሻሻል ነው፡፡

**አንቀጽ 3. የመመሪያው አስፈላጊነት**

ሀ.ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው መብታቸው ተከብሮላቸው፣ በአንፃሩ ግዴታቸውንም ተረድተው ኃላፊነታቸውን በብቃት በመወጣት በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሣታፊ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል፣

ለ. የሥነ-ምግባር ግድፈቶች አጠቃላይ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ከመጉዳት አልፈው የቤተሰብ፣ የህብረተሰብና የሀገር ችግር ከመሆናቸው አስቀድሞ ቅድመ-መከላከል ሥራ መሥራት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ሐ. ተማሪዎች በጥሩ ሥነ-ምግባር ታንፀው በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጭ የግልና የጋራ ተሳትፎን በማሳደግ ለትምህርት ቤት፣ ለህዝብ ሀብትና ንብረት የባለቤትነትና የተቆርቋሪነት ስሜት እንዲያዳብሩና በተለያዩ ተግባራት በሚያደርጉት ተሳትፎ በኃላፊነት ስሜት እንዲወጡ ለማስቻል ይህ መመሪያ አስፈላጊ ነው፡፡

## **አንቀጽ 4. የተፈፃሚነት ወሰን**

4.1. ይህ መመሪያ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ትምህርት ሴክተር ከቅድመ-አንደኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በመደበኛውም ሆነ በማታው የትምህርት ፕሮግራሞች በመማር ላይ በሚገኙ በመንግሥት፣ በመንግሥታዊ ባልሆኑ እና በግል የትምህርት ተቋማት ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

4.2. የዚህ መመሪያ የተፈጻሚነት ወሰን በትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ እና ከትምህርት ቤቶች ውጭ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ ያለውን አካባቢንም ያካትታል፡፡

4.3. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸ ቃል ሁሉ ለሴት ያታም ያገለግላል፡፡

## **አንቀጽ 5. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የተማሪዎች የሥነ-ምግባር መመሪያ ውስጥ የያዘው ትርጉም፡-

5.1 **የክፍል ኃላፊ መምህር** ማለት ተጠሪ ለሆነበት ክፍል የተቃና የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር የሚያስተባብር መምህር ነው፡፡

5.2 **ዩኒት መሪ ወይም ፈረቃ አስተባባሪ** ማለት ተጠሪነቱ ለአካዳሚክ ምክትል ርዕሠ-መምህር ሆኖ የፈረቃውን አካዳሚክና አስተዳደራዊ ሥራዎችን የሚያስተባብር መምህር ነው፡፡

5.3 **የትምህርት ቤት ዲስፒሊን ኮሚቴ** ማለት በትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን የቀላል ዲስፕሊን ክስ ውሳኔ የሚሰጥና የከባድ ዲስፕሊን ክስ ሲቀርብ የውሳኔ ሀሳብ ለርዕሠ-መምህሩ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው፡፡

5.4 **የትምህርት ተቋም** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 3 ለትምህርት ቢሮ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተቋቋመ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆነና የግል አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ፣ ቅድመ-አንደኛ፣ መጀመሪያ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡

5.5 **የትምህርት እርከን** ማለት በአጠቃላይ የትምህርት ዘርፍ ቅድመ-አንደኛ፣ የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ደረጃን የሚገልጽ ስያሜ ነው፡፡

5.6 **ትምህርት ቢሮ** ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመ የአስፈፃሚ አካል የሆነ መሥሪያ ቤት ነው፡፡

5.7 **ሥነ-ምግባር** ማለት በእያንዳንዱ የትምህርት ተቋም ወይም ማህበረሰብ ውስጥ ስህተት ወይም አላስፈላጊ የሆኑት ድርጊቶች ወይም ተግባሮች እንዳይፈጸሙ፣ ትክክል ወይም አስፈላጊ የሆኑት ደግሞ እንዲፈጸሙ የሚያስችል ነው፡፡

5.8 **የዲስፒሊን ጥፋት** ማለት በተማሪዎች ሥነ-ሥርዓት መመሪያ የማይፈጸሙ ሆነዉ ተደንግገው የተቀመጡ ድርጊቶችን መፈፀም ወይም በመመሪያው እንዲፈፀሙ የተቀመጡ ግልፅና ሕጋዊ የሆኑ ተግባራትን አለመፈፀም ወይም አለማድረግ ማለት ነው፡፡

5.9 **የዲስፒሊን ጥፋት ውሣኔ** ማለት አንድ ተማሪ በፈፀመው የዲሲፕሊን ጥፋት መሠረት የሚሰጥ ተመጣጣኝ ውሣኔ ነው፡፡

5.10 **የምርጦች መዝገብ** ማለት ከሥነ-ምግባር ጋር በተያያዙ ተግባራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ተማሪዎች የሚመዘገቡበት ነው፡፡

5.11 **የሥነ-ምግባር ግድፈት መከታተያ መዝገብ** ማለት ጥፋት የፈፀመ ተማሪ ለፈፀመው ድርጊት ከወላጅ ጋር በመሆን ኃላፊነት ወስደው ተማሪው ጥፋቱን እንዳይደግም በመስማማት የሚፈርሙበት መዝገብ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት
# የተማሪው መብትና ግዴታ

መልካም ዜጎችን ለማፍራት በትምህርት ቤት ውስጥ በሚደረገው ጥረት ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባቸው ሥነ-ሥርዓቶችና ደንቦች በግልጽ ተለይተው ሊቀመጡና በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እንዲሁም በተማሪዎችም ጭምር ሊታወቁና ሊከበሩ ይገባል፡፡ስለሆነም ተማሪዎች የሚከተሉትን መብቶች ማወቅና ግዴታዎችን ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 6. የተማሪው መብት

ተማሪው፡-

6.1 በመማር ማስተማሩ ሂደት ጠይቆ የመረዳት፣

6.2 ጥራት ያለው፣ ፍትሀዊና ተገቢ የሆነ ትምህርት የማግኘት፣

6.3 መምህሩን የመገምገም፣

6.4 በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በሚያጋጥማቸው ጉዳይ መረጃ የመስጠትና ችግሮችን በዉይይትና በሰላማዊ መንገድ የመፍታት፣

6.5 በትምህርት ግብአቶች የመጠቀምና አገልግሎት የማግኘት፣

6.6 በልዩ ልዩ የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞች የመሳተፍ፣

6.7 ለመማር ምቹ የሆነ፣ አድልዎ፣ ማግለልና ጥቃት በሌለበት ትምህርት ቤት የመማር፣

6.8 ከመምህራን ጋር መልካም የሆነ የመማር ማስተማር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍና እርዳታ የማግኘት፣

6.9 ለህብረተሰቡ ጠቃሚ በሆኑ ተግባራት ላይ በያገባኛል ስሜት የመሳተፍ፣

6.10 በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎችን ተሣትፎ በሚጠይቁ አደረጃጀቶች በንቃት የመሳተፍ፣

6.11 የተማሪ ፓርላማ አባላትን፣ መማክርትንና የክፍል አለቆችን የመምረጥና የመመረጥ፣

6.12 የተለያዩ የሀገሪቱንና የክልሉን ሕጎችና ደንቦችን የማወቅ፣ ለምሳሌ፡- የትራፊክ ደህንነት፣ የአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ፣...ወዘተ

6.13 በተማሪዎች ላይ በሚወሰዱ የሥነ-ምግባር ጥፋት ርምጃዎች ዉሳኔ ላይ በተወካዮቻቸው አማካይነት የመሳተፍና አስተያየት የመስጠት፣

6.14 በትምህርት ቤት ዉስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ዉጭ ማለትም ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ከትምህርት ቤት ሲመለሱ ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ የመመላለስ፣

6.15 የትምህርት ውጤቶቻቸውን የማየት፣ የማወቅ እና ቅሬታ ሲኖራቸው የማቅረብ፣

6.16 የትምህርት ቤቱ ዓመታዊና ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ላይ የመሳተፍና ዕቅዶቹን የማወቅ፣ የማሳወቅና አስተያየት የመስጠት፣

6.17 በትምህርት ቤት የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚደግፉ የፈጠራ ሥራዎች የመሣተፍ፣

6.18 በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የአከባቢ ጥበቃ ሥራዎችን የመሥራት፣

6.19 የትምህርት ቤቱ ተማሪ መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ ከትምህርት ቤቱ የማግኘት፣

6.20 በክልሉ ለትምህርት ደረጃው ከተደነገገው ሥርዓተ-ትምህርት ውጪ የሆኑ ይዘቶች ያሉትን ትምህርቶች ያለመማር መብቶች ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ 7. የተማሪው ግዴታ

ተማሪው፡-

7.1. በትምህርት ካለንደር መሠረት በወቅቱ ትምህርት ቤት ተገኝቶ የመመዝገብና ትምህርቱን የመከታተል፣

7.2. ለትምህርት ከተመደቡት የትምህርት ቀናት ያለበቂ ምክንያት ከትምህርት ገበታ አለመቅረት፣

7.3. የመማሪያ መጻህፍት በክፍል ይዞ በመገኘት የመጠቀም፣

7.4. በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ በመምህሩ የሚሰጠውን ትምህርት በጥሞና የመከታተል፣ መልመጃዎችን፣ የቤት ሥራዎችንና የችሎታ መመዘኛዎችን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ሠርቶና አጠናቅቆ የማቅረብ/የማስረከብ፣

7.5. ከትምህርት ቤቱ አመራር፣መምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የሚሰጡትን ድጋፍ፣ ምክርና መመሪያ የመፈፀም፣

7.6. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት ሞባይል ስልክ፣ አይፖድና መሰል ሙዚቃ ማዳመጫ፣ ታብሌት፣ ስማርት ሰዓት እና ቪዲዮ ማጫወቻዎችን በፍጹም ይዞ አለመገኘት፣

7.7. በትምህርት ቤቱ የኮምፒዩተር ወይም አይቲ ማዕከል ከትምህርት ድረ-ገጽ ውጪ አለመጠቀም፣

7.8. የተማሪዎችና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ሰብአዊ መብት የማክበር፣ ለምሳሌ፡- ያታዊ ትንኮሳ አለማድረግ፣ አለማሸማቀቅ፣ አለመስደብ፣ ፀብ አለመጫር፣

7.9. የትምህርት ቤቱ ግቢ ውብ፣ ጽዱ፣ ምቹና ማራኪ እንዲሆን የመንከባከብ፣ ለምሳሌ፡- ቆሻሻ ያለቦታው አለመጣል፣ ከመፀዳጃ ውጪ አለመፀዳዳት፣

7.10. ከትምህርት ቤቱ የተዋሱዋቸውን የመማሪያ መጻህፍትንና ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎችን በጥንቃቄ የመያዝና በአግባቡ የመጠቀም እና በወቅቱ የመመለስ፣ በመጽሐፎቹ ላይም ሆነ ውስጡ ጽሁፎችን አለመጻፍ፣ ገጾችን አለመቅደድ፣ አለመገንጠል፣

7.11. ለትምህርት ቤቱ አመራርና መምህራን ማለትም ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ተገቢውን አክብሮት የመስጠት፣

7.12. ብሔርን፣ ፆታን፣ ሃይማኖትን፣ ፖለቲካ አስተሳሰብን፣...ወዘተ መነሻ ያደረገ አድማ/ግጭት አለመፈፀም፣

7.13. ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመግባባትና በመተሳሰብ የመሥራትና የመማር፣

7.14. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የማንኛውንም ዓይነት ሃይማኖት የአምልኮ ሥርዓት እና የፖለቲካ ቅስቀሳ አለማካሄድ፣

7.15. በት/ቤት ቅጥር ግቢ ማንኛውንም በአካልና በጤና ጉዳት የሚያደርስ መሣሪያ ይዞ አለመገኘት፣

7.16. የትምህርት ቤቱን ዩኒፎርም (ደንብ ልብስ) በትምህርት ቤቱ በታወቀና በተፈቀደ ዲዛይን መሠረት አሰፍቶ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እና ወደ ቤት ሲመለስ የመልበስ እና

ንፅህናውንም የመጠበቅ፣ ትምህርት ቤቶችም የልብስ ዲዛይን አዘጋጅተዉ ለተማሪዎቻቸዉ መስጠት አለባቸዉ፤

7.17. ሥነ-ሥርዓትን የተከተለ ማለትም በትምህርት ቤቱ የታወቀና የተፈቀደ አለባበስ፣ የፀጉር አቆራረጥ፣ አሠራር እና የአካል ንፅህና የመጠበቅ፣

7.18. ከትምህርት ቤቱ እውቅና ውጪ በዓላትን አለማክበር፣ ገንዘብ አለማዋጣት፣ ለሽርሽርና ሌሎች ትምህርታዊም ሆነ ትምህርታዊ ያልሆኑ የመዝናኛ ጉዞዎችን አለማካሄድ፣

7.19. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አስፈላጊ ያልሆኑና የኢትዮጵያዊነት ባህል የማይገልፁ ቀናትን ለምሳሌ፡- Color Day, Crazy Day, Valentine Day …ወዘተ አለማክበር፣ እንዲከበርም አለማስተባበር፣ አለመተባበር፣

7.20. በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ በማንኛውም አድማ ላይ አለመሣተፍ፣ ጠብ አጫሪነት ድርጊት አለመፈፀም፣

7.21. በትምህርት ሰዓት ያለ በቂ ምክንያት በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ አለመዟዟር፣

7.22. በአጥር ዘሎ አለመግባት፤ አለመውጣት፣

7.23. በትምህርት ቤት ግቢና ከትምህርት ቤት ውጪ ሲጋራ አለማጨስ፣ ጫትና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን አለመጠቀም፣

7.24. በትምህርት ቤት ግቢና ከትምህርት ቤት ውጪ ስርቆት አለመፈጸም፣ ቁማር አለመጫወት፣ እንዲሁም በሌሎች ህገ-ወጥ ድርጊቶች አለመሣተፍ፣

7.25. በህገ-ወጥ የሕፃናት ዝውውር፣ ሕፃናትንና ሴት ተማሪዎችን በሚጎዳ ተግባር ላይ አለመሣተፍ፣ አገናኝ ሆኖ አለመሥራትና አለመተባበር፣

7.26. በሰንደቅ ዓላማ ሥነ-ሥርዓት ላይ በሰዓቱ በመገኘት የማክበር፣ ለምሳሌ፡- መሰለፍ፣ ብሔራዊ መዝሙር መዘመር፣ የሚተላለፉ መልእክቶችን በጥሞና የማዳመጥ፣

7.27. ማንኛውንም የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ስም የሚያጎድፍ እና በትምህርት ቤቱ ያልተፈቀዱ ጽሁፎችን በየትኛውም ሥፍራ አለመጻፍ፣ አለመለጠፍ፣

7.28. በትምህርት ቤት ንብረት ማለትም ኮምፒዉተሮችን፣ ፕላዝማ፣ ሬዲዮ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ የስልክና የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ የኤሌክትሪክ መብራት ማብሪያና ማጥፊያ፣ የውኃ ቧንቧ፣ መፀዳጃ ቤቶችን፣ የመቀመጫ ወንበሮችንና

ዴስኮችን፣ መማሪያ ክፍሎችን፣ ምድረ-ግቢውንና ሌሎች ግብአቶችን...ወዘተ በአግባቡና በጥንቃቄ የመጠቀም፣ የመጠበቅ፣ የመንከባከብ፣ ተበላሽቶ ሲገኝ ሪፖርት የማድረግ፣

7.29. በሣይንስ ቤተ-ሙከራዎች ያለ መምህሩ ወይም ከቤተ-ሙከራ ባለሙያ ፈቃድ ውጪ ኬሚካሎችንና አፓራተሶችን አለመጠቀም፣

7.30. ወላጅ አጥ የሆኑ፣ ኤች አይቪ በደማቸው ያለባቸው፣ አካል ጉዳተኞችንና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች፣ መምህራንንና ሌሎች ሠራተኞችን አለማግለል፣ ድጋፍ የማድረግ፣

7.31. በትምህርት ቤት ግቢም ሆነ ከትምህርት ቤት ወጭ ከመምህራንና ከትምህርት ቤቱ አመራርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት አለመፍጠር፣ ለምሳሌ፡- ጫት አብሮ አለመቃም፣ መጠጥ አብሮ አለመጠጣት፣ ለፆታዊ ትንኮሳ በሚያጋልጥ ሁኔታና በመሳሰሉት አለመሳተፍ፣

7.32. ወላጅ/አሳዳጊ እንዲያመጣ ሲጠየቅ በወቅቱ የማምጣት፣

7.33. የመማር ማስተማር ሂደትና ሌሎችን የትምህርት ቤት ተግባራትን አለማወክ፣ ለምሳሌ፡- መምህር በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ሲያስተምር፣ በቤተ-መጻህፍት ውስጥ ሌሎች ተማሪያዎች ሲጠቀሙ፣ ማጠናከሪያ ትምህርት ሲሰጥ፣ እንዲሁም የትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ስብሰባ ሲካሄድ፣...ወዘተ አለማወክ

7.34. ፈተናን መኮረጅ፣ ማስኮረጅ፣ መስረቅ እና ማሰረቅ ተግባር አለመፈፀም እና ተባባሪ አለመሆን፣ እንዲሁም ተግባሩን የሚፈፅሙ አካላትን የማጋለጥ፣

7.35. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥም ሆነ ውጭ የትምህርት ቤት መታወቂያ ሁል ጊዜ ይዞ የመገኘት፣

# ክፍል ሶስት

# የሥነ-ምግባር ጥሰቶችና መወሰድ የሚገባቸው የዲስፕሊን እርምጃዎች

## አንቀጽ 8. የዲስፕሊን እርምጃ ሊያስወስዱ የሚችሉ የጥፋት ዓይነቶች

### 8.1. ቀላል የዲስፕሊን እርምጃ ዓይነቶችን የሚያስከትሉ ጥፋቶች

8.1.1. ትምህርት ቤት አርፍዶ የመጣ፣ ያለፈቃድ ቀድሞ የወጣ፣

8.1.2. የቤት ሥራና የክፍል ሥራ እንዲሁም መልመጃዎችን በወቅቱ ሠርቶ ያላስረከበ፣

8.1.3. በትምህርት ሰዓት ከትምህርት ገበታ ውጭ የተገኘ፣

8.1.4. የመማሪያ መፃህፍትንና ሌሎች የመማሪያ ቁሳቁሶችን በትምህርት ገበታው ይዞ ያልተገኘ፣

8.1.5. የሌላ ተማሪ ንብረት መስረቅ ወይም መቀማት፣

8.1.6. ሥነ-ሥርዓት በጎደለ ሁኔታ ማለትም ትምህርት ቤቱ ከፈቀደው አለባበስ ውጪ በሆነ ሁኔታ የደንብ (ዩኒፎርም) ለብሶ፣ ፀጉር አስቀርጦ ወይም ተሠርቶ የተገኘ፣

8.1.7. የትምህርት ቤቱን አትክልት፣ ዛፎች፣ አበባዎች፣ ፍራፍሬዎች፣ እና ሌሎችንም የነቀለ፣ የቆረጠ፣ የቀጠፈ፣

8.1.8. በትምህርት ቤቱ ብልሹ አሠራር ወይም ድርጊት ሲፈፀም ተመልክቶ ያላጋለጠ ወይም በተባባሪ ድርጊት ፈፃሚነት በቸልታ ያለፈ፣

8.1.9. የትምህርት ቤቱን ንብረት በአግባቡ ያልተጠቀመ፣ ማለትም ጥንቃቄ በጎደለው አያያዝ የያዘ፣ እንዲሰበር ወይም እንዲበላሽ ያደረገ፣

8.1.10. በዚህ ንኡስ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ቀላል የጥፋት ዓይነቶች ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያላቸውን ጥፋቶች መፈፀም ናቸው፡፡

## 8.2. ከባድ የዲስፕሊን እርምጃ ዓይነቶችን የሚያስከትሉ ጥፋቶች

8.2.1. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 8.1 ላይ የተዘረዘሩትን ቀላል የሥነ-ምግባር ጥፋቶችን ሲፈጽም ተገኝቶ ከተቀጣ በኋላ እንደገና በድጋሚ የፈፀመ፣

8.2.2. በአጥር ሾልኮ የገባ፣ የወጣ፣

8.2.3. በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚከናወነውን የመማር ማስተማር ሥራን ያወከ፣

8.2.4. የሀሰት የምስክርነት ቃል የሰጠ ወይም በውሸት ለመክሰስ የሞከረ ወይም የሀሰት ክስ መሥርቶ ተከሳሽን ተጠያቂ ያደረገ፣

8.2.5. ግጭት ወይም አድማ ቀስቃሽ የሆኑ ግጥሞች፣ ሥነ-ጽሁፎች፣ ዖታዊ ትንኮሳ የያዙ ምስሎች፣...ወዘተ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ይዞ የተገኘ፣ ያሳየ፣

8.2.6. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ማንኛውንም ዓይነት ሞባይል ስልክ፣ አይፓድ እና መሰል ሙዚቃ ማዳመጫ፣ ታብሌት፣ ስማርት ሰዓት፣ ቪዲኦ እና...ወዘተ ይዞ የተገኘ፣

8.2.7. በትምህርት ቤቱ የኮምፒዩተር ማዕከል ከትምህርት ውጪ የሆኑ ሙዚቃ፣ መዝሙርና ፊልሞችን ጌሞችን ወይም ጨዋታዎችን ያዳመጠ፣ የተመለከተ፣ የተጫወተ፣

8.2.8. መምህራንንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የሰደበ፣ የዛተ፣ ያስፈራራ፣ ፀብ የጫረ፣ የተተናኮሰ፣

8.2.9. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እና ውጭ አስፈላጊ ያልሆኑና የኢትዮጵያዊነት ባህል የማይገልፁ ቀናትን (Color Day, Crazy Day, Valentine, ...etc) ያከበረ፣ እንዲከበር ያስተባበረ፣ የተባበረ፣

8.2.10. የሰንደቅ ዓላማ ሥነ-ሥርዓት እንዳይከበር ያወከ፣ ለምሳሌ፡- በሰልፍ ሥነ-ሥርዓት ወቅት ተማሪዎችን የረበሸ፣ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣ ወይም ሲወርድ ከሰልፍ ውጪ ሆኖ በድምጽ ያወከ፣ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና ሲወርድ ቆሞ ለሰንደቅ ዓላማ ክብር መስጠት ሲገባው የተራመደ፣

8.2.11. በቤተ-መጻህፍት ውስጥ በሚገኙ መጻህፍትም ሆነ በመማሪያ መጻህፍት ጽሁፎችና ገጾች ላይ ያሰመረ፣ ሥዕል የሣለ፣ የመጻህፍቱን ገጽ የቀደደ፣ የገነጠለ፣

8.2.12. የትምህርት ቤት ንብረት ማለትም ፕላዝማ፣ ሬዲዮ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ የስልክና የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ የኤሌክትሪክ መብራት ማብሪያና ማጥፊያ፣ የውኃ ቧንቧ፣ መፀዳጃ ቤቶችን፣ የመቀመጫ ወንበሮችንና ዴስኮችን፣ መማሪያ ክፍሎችን፣ ምድረ-ግቢውንና ሌሎችንም የትምህርት ግብአቶች በጥንቃቄ ያልተጠቀመ፣ ያበላሸ፣ የሰበረ፣ ሌሎች ሲያበላሹ ወይም ሲሰብሩ አይቶ በተባባሪነት በቸልታ ሪፖርት ሳያደርግ ያለፈ፣

8.2.13. ሰብአዊ ክብር የሚነኩ ተግባራትን የፈፀመ፣ ለምሳሌ፡- የአንድን ሰው ፆታ ወይም ተክለ-ሰውነት ወይም አለባበስ በተመለከተ አሉታዊ መገለጫዎች በመስጠት ያጣጣለ፣ ቁጣ ቀስቃሽ ቅፅል ስሞችን የተጠቀመ፣...ወዘተ

8.2.14. ፆታን መሠረት በማድረግ የሚያንቋሽሹ ጽሁፎችን፣ መጽሔቶችን፣ ምስሎችንና ቪዲዮችን ወደ ትምህርት ቤት ይዞ የመጣ፣ ለሌሎች ያሳየ፣ እንዲሁም በግድግዳ ላይ የለጠፈ፣

8.2.15. ፈተና መኮረጅና ማስኮረጅን በተመለከተ፡-

ሀ) በጎን፣ ወደ ፊትና ወደ ኋላ ተንቀሳቅሶ የኮረጀ፣ ያስኮረጀ፣ (በማንኛዉም መልኩ የኮረጀ/ያስኮረጀ)

ለ)ከመጻህፍት፣ ከማስታወሻ ደብተር እንዲሁም ለመኮረጅ አቅዶ አጫጭር ጽሁፎችን ተጠቅሞ የኮረጀ፣ ያስኮረጀ፣

8.2.16. አደንዛዥ ዕፅ፣ ጫት፣አልኮል መጠጥ፣ ሲጋራ፣...ወዘተ በትምህርት ቤት ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ የተጠቀመ፣

8.2.17. በተማሪዎች እና በአጠቃላይ በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ስለታማ፣ የጦር መሣሪያ፣ የመሳሰሉትን በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ይዞ ለመግባት የሞከረ፣ ይዞ የተገኘ፣

8.2.18. ሴት ተማሪዎችን የዘለፈ፣ የሰደበ፣ የዛተ፣ ያስፈራራ፣

8.2.19. የራሱንም ሆነ የሌሎች ተማሪዎች የትምህርት ማስረጃ የሠረዘ፣ የደለዘ፣ የቀደደ፣ያቃጠለ፣

8.2.20. በትምህርት ቤት ግቢ የማንኛውንም ዓይነት ሃይማኖት የአምልኮ ሥርዓት እና የፖለቲካ ቅስቀሳ ያካሄደ፣

8.2.21. የትምህርት ቤት መገልገያ ቁሳቁሶችን የሰረቀ፣ ያሰረቀ፣ እንዲሰረቅ ያስተባበረ፣ የተባበረ፣ ወይም ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ፣

8.2.22. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ለወሲብ ተግባር ሴት ወይም ወንድ ተማሪዎችን ለማግባባት የሞከረ፣ ያግባባ፣ ያስተባበረ፣ ወሲብ ቀስቃሽ የሆኑ ጽሁፎችንና ፖስተሮችን ያሰራጨ፣ የለጠፈ፣

8.2.23. በደማቸው የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ያለባቸውን፣ ወላጅ-አጥ የሆኑትን፣ አካል ጉዳትና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች፣ መምህራንና ሠራተኞች ያንቋሸሸ፣ ያገለለ፣ ያሸማቀቀ፣

8.2.24. ሴት ተማሪን አስገድዶ የደፈረ፣ አካላዊ ጥቃት ያደረሰ፣

8.2.25. ሴት ልጅ የጠለፈ/ያስጠለፈ

8.2.26. ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በመጠቀም መድረስ ወደ ሌለበት የትምህርት ደረጃ የደረሰ፣

8.2.27. በህገ ወጥ መንገድ ሕፃናትን በማዘዋወር ተግባር የተሳተፈ፣ ሕፃናትንና ሴት ተማሪዎችን በሚጎዳ ተግባር ላይ እንዲሣተፉ ያደረገ፣ የደለለ፣ ከትምህርት ቤት ያስኮበለለ፣ ከሚያስኮበልሉ/ከሚደልሉ ጋር የተባበረ፣

8.2.28. ፈተና መስረቅ፣ ማሰረቅና ተባባሪ መሆንን በተመለከተ

ሀ) ፈተና ለተፈታኝ ተማሪዎች እስኪሠራጭ ድረስ ከተቀመጠበት ቦታ ወይም ክፍል የሠረቀ፣ ያስሠረቀ፣ ያሠራጨ፣ የተባበረ፣

ለ) ለሌላ ተማሪ የተፈተነ፣ ሌላ ተማሪ እንዲፈተንለት የፈቀደ፣

ሐ)የፈተና መልስ ካልነገርከኝ/ካልሰጠኸኝ በማለት በፈተና አዳራሽ ከተፈታኝ ተማሪ የመልስ ወረቀት የነጠቀ፣ በፈተና አዳራሽ ውስጥም ሆነ ውጭ ያስፈራራ፣ የዛተ፣ ጫና የፈጠረ፣ የፈተና ሥርዓትን ያወከ፣

መ) የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የኮረጀ/ያስኮረጀ

8.2.29. በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ላይ ሰብአዊ መብት ጥሰት፣ አካል ማጉደልና የሕይወት ማጥፋት ድርጊቶችን/ጥፋቶችን የፈፀመ፣

8.2.30. ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት ታዉሶ ወስዶ ያልመለሰ፣

## አንቀጽ 9. ለጥፋት ዓይነቶች የሚወሰዱ የዲስፕሊን እርምጃ ዓይነቶች

### 9.1. ለቀላል የጥፋት ዓይነቶች የሚወሰዱ የእርምጃ ዓይነቶች

ማንኛውም ተማሪ ከላይ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8.1 ላይ ከ8.1.1 እስከ 8.1.10 የተጠቀሱትን ተመሳሳይ ክብደት ያላቸውን ቀላል የሥነ-ምግባር ጥሰቶችን የፈፀመ እንደሆነ በየትምህርት እርከኑ ተለይተው ከተጠቀሱት የእርምጃ ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

#### 9.1.1. በቅድመ-አንደኛ ላይ የሚገኙ ሕፃናት

በዚህ የትምህርት እርከን ለሚገኙ ሕፃናት/ተማሪዎች ለፈጸሙት ቀላልና ከባድ ጥፋቶች የሚወሰደው የእርምጃ ዓይነቶች ህፃናቱ/ተማሪዎቹ ከስህተታቸው እንዲማሩ በአመቻች መምህር በኩል ማስተማርና መምከር ብቻ ይሆናል፡፡

#### 9.1.2. ከ1ኛ-6ኛ ትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ሕፃናት ወይም ተማሪዎች

ሀ) ጥፋቱን በቅድሚያ ተረድቶ እንዲጸጸት ዕድል መስጠት፣

ለ) ከሚወደው ወይም በፍላጎቱ ከሚያዘውትራቸው ጫወታዎች (ስፖርት…ወዘተ) ላይ ለአንድ ሣምንት መከልከል፣

መ) ለወላጆቻቸው ጥፋቱን በማሳወቅ እንዲመክሩት ማድረግ፣

ሠ) የቃል ማስጠንቀቂያ በመስጠት መዝግቦ መያዝ፣

#### 9.1.3. ከ7ኛ-8ኛ ትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች

ሀ) በቃለ-ጉባኤ የተደገፈ የቃል ማስጠንቀቂያ፣

ለ) ከሚወደው ወይም በፍላጎቱ ከሚያዘውትራቸው ጫወታዎች (ስፖርት…ወዘተ) ላይ ለአንድ ሣምንት መከልከል፣

መ) ለወላጆቻቸው ጥፋቱን በማሳወቅ እንዲመክሩት ማድረግ፣

መ) ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ በሥነ-ምግባር ግድፈት መከታተያ መዝገብ ላይ በመመዝገብ ለወላጆች አሳውቆ እንዲታረም ማድረግ፣

### 9.1.4. ከ9ኛ-12ኛ ትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች

ሀ) በቃለ ጉባኤ የተደገፈ የቃል ማስጠንቀቂያ፣

ለ) ለወላጅ አሳውቆ ለፈጸመው ጉዳት ወይም ጉድለት ማካካሻ እንዲተካ ማድረግ፣

ሐ) ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ለወላጆች አሳውቆ በሥነ-ምግባር ግድፈት መዝገብ በመመዝገብ እንዲታረም ማድረግ፣

## 9.2. ለከባድ የጥፋት ዓይነቶች የሚወሰዱ የእርምጃ ዓይነቶች

ማንኛውም ተማሪ ከባድ የሥነ-ምግባር ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ በመደበኛ ህግ መሠረት የሚጠየቅበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ጥፋቱ ቅለትና ክብደት በየትምህርት እርከኑ የተለያዩ የእርምጃ ዓይነቶች ውስጥ አንዱ በሚመለከተው ክፍል ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 9.2.1. ከ1ኛ-6ኛ ትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ህፃናት/ተማሪዎች

ሀ) ከሚወደው ወይም በፍላጎቱ ከሚያዘውትራቸው ጫወታዎች (ስፖርት…ወዘተ) ላይ ለሁለት ሣምንታት መከልከል፣

ለ) ጥፋቱን ለወላጅ አሳውቆ እንዲታረም ማድረግና መመዝገብ፣ ሆኖም ግን የተማሪው ዕድሜ ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ወይም ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ትምህርት እርከን ካሉ ተማሪዎች ዕድሜ ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደጥፋቱ ቅለትና ክብደት ለነዚህ የትምህርት እርከኖች ከተደነገጉት ከባድ የእርምጃ ዓይነቶች ውሣኔዎች ውስጥ አንዱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 9.2.2. ከ7ኛ-8ኛ ትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች

ሀ) ለፈጸመው ጉዳት/ጉድለት ማካካሻ እንዲተካ ማድረግ፣

ለ) ወላጅ ወይም አሳዳጊ በተገኘበት ተግሳፅ ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በስነ-ምግባር ግድፈት መከታተያ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣

ሐ) ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታ ማገድና ሌላ ትምህርት ቤት ሄዶ እንዳይማር ማድረግ (በአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 8.2.18 እስከ 8.2.26 ድረስ የተጠቀሱትንና ተዛማጅ የሆኑትን ጥፋቶች ፈጽመው ሲገኙና የፈጸሙት ጥፋት በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እና በመማር ማስተማር ሂደት ያስከተለው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚ ይሆናል)፣

### 9.2.3. ከ9ኛ-12ኛ ትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች

ሀ) ለፈጸመው ጉዳት/ጉድለት ማካካሻ እንዲተካ ማድረግ፣

ለ) ወላጅ/አሳዳጊ በተገኘበት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በሥነ-ምግባር ግድፈት መዝገብ ላይ መመዝገብ፣

መ) ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታ ማገድና የእገዳው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ሌላ ቦታ ሄዶ እንዳይማር ማድረግ፣(ይህም ውሣኔ ከላይ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ ከ8.2.1 እስከ 8.2.17ድረስ የተጠቀሱትንና ተዛማጅ የሆኑትን ጥፋቶች ፈጽመው ሲገኙና የፈጸሙት ጥፋት በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በመማር ማስተማሩ ሂደት ያስከተለው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚ ይሆናል)፣

ሠ) ለሁለት ዓመት ከትምህርት ገበታ ማስወገድና የእገዳው ጊዜ እስከሚያበቃ ድረስ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ሄዶ እንዳይማር ማድረግ፣(ይህም ውሣኔ ከላይ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ ከ8.2.18 እስከ 8.2.26 ድረስ የተጠቀሱትንና ተዛማጅ የሆኑትን ጥፋቶች ፈጽመው ሲገኙና የፈጸሙት ጥፋት በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በመማር ማስተማሩ ሂደት ያስከተለው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡)

ረ) ከትምህርት ቤት እስከ መጨረሻው ማስወገድ እና በጥፋቱ በመደበኛ ፍርድ ቤት እንዲጠየቅ ማድረግ ይሆናል፡፡(ይህም ውሣኔ ከላይ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 8.2.25 እስከ 8.2.27 ድረስ የተጠቀሱትንና ተዛማጅ የሆኑትን ጥፋቶች ፈጽመው ሲገኙና የፈጸሙት ጥፋት በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና በመማር ማስተማሩ ሂደት ያስከተለው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝ ተፈፃሚ ይሆናል)፡፡

### 9.2.4. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሞባይል ስልክን ሲጠቀም የተገኘ ተማሪ ላይ የሚወሰድ የዲስፒሊን ርምጃን

ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለመማርና ለተለያዩ መዝናኛና ማህበራዊ ግንኙነቶች የሚውሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለምሳሌ፡- ሞባይል ስልክ፣ አይፓድ እና መሰል ሙዚቃ ማዳመጫ፣ ታብሌት፣ ስማርት ሰዓት፣ ቪዲኦ ማጫወቻና የመሳሰሉት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ይዘው ሲገኙ የሚሰጠውን ትምህርታቸውን በትኩረት እንዳይከታተሉ፣ ቤተ-ሙከራ ገብተው እንዳይለማመዱ ወይም እንዳይሠሩ፣ ቤተ-መጽሐፍት ገብተው የተለያዩ ማጣቀሻ መጻህፍትን እንዳይጠቀሙ፣ ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን የቡድን ሥራዎችን እንዳይሠሩና እንዳያጠኑ፣ ተማሪዎች እርስ በርስ በክፍል ያገኙትን ዕውቀት እንዳያዳብሩና እንዳይደጋገፉ፣ ውድ እና በሕይወታቸው መልሰው የማያገኙትን የትምህርት ጊዜያቸውን እየተሻማባቸው በመሆኑ ሥርዓት መዘርጋት አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት ከላይ የተጠቀሱትን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይዘው ቢገኙ ለጥፋቱ ከላይ የተጠቀሰው ርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በወቅቱ ሲጠቀሙበት የነበሩት የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የትምህርት ቤቱን ሥርዓት በሚያስከብር አካል ተወስዶ ለትምህርት ቤቱ ለዚሁ በተዘጋጀው ህጋዊ መዝገብ ተመዝግቦ ገቢ ሆኖ እስከ ዓመቱ መጨረሻ እንደተያዘ ይቀመጣል፡፡ በዓመቱ መጨረሻም በወላጅ በዓል ቀን የተማሪው ጥፋተኝነት በግልጽ ተነግሮ እና በሥነ-ምግባር ግድፈት መከታተያ መዝገብ ተመዝግቦ

ለወላጁ ይመለሳል፡፡ ይህንንም ድርጊት በድጋሚ ከፈጸመ ሙሉ በሙሉ ተወርሶ ለትምህርት ቤቱ ንብረት ክፍል በሞዴል 19 ገቢ በማድረግ ለትምህርት ቤቱ አገልግሎት እንዲውል ይደረጋል፡፡

9.2.5. **ፈተና መኮረጅ፣ ማስኮረጅ፣ መስረቅ፣ ማሰረቅና ተባባሪ መሆን**

ፈተና ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ዓመቱን ሙሉ የለፉበትና የደከሙበት የሥራቸው ውጤት የሚለካበትና ከክፍል ወደ ክፍል ማለፍ የሚያስችል እንዲሁም በክልላዊና በብሔራዊ ፈተናዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር የሚወዳደሩበት መሣሪያ ነው፡፡ የፈተና አስተዳደር፣ አያያዝና ሥርጭት ብርቱ ጥንቃቄ የሚያሻ ከመሆኑም በላይ ተማሪዎች ተረጋግተው ምንም የህሊና መረበሽ ሳያጋጥማቸው መፈተን እንዲችሉ ከትምህርት ቤት ጀምሮ በየደረጃው ያሉት የትምህርት ባለሙያዎች፣ የትምህርት ቤቱ ባለድርሻ አካላት፣ የፍትህ አካላት እና መላው ማህበረሰብ የበኩሉን መወጣት እንዳለበት ይታመናል፡፡ በመሆኑም፡-

ሀ) ፈተና በመኮረጅና በማስኮረጅ የሚወሰድ የእርምጃ ዓይነት፡- ከመጻህፍትና ከማስታወሻ ደብተር እና አጫጭር ጽሁፎችን በማዘጋጀት እና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን ለኩረጃ የተጠቀመ ወይም ፈተናን የጎንዮሽ የኮረጀ፣ ያስኮረጀ ተማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲኮርጅ/ሲያስኮርጅ የተገኘበት የፈተና ውጤት ይሰረዛል፣ ወላጅ እንዲያውቀውም ይደረጋል፡፡ ጥፋቱ ሲደገም ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታው ይታገድና በዚያው የትምህርት ዘመን ሌላ ትምህርት ቤት ሄዶ እንዳይማር ይደረጋል፡፡

ለ) ፈተና በመስረቅ፣ በማሰረቅና ተባባሪ በመሆን ለሚሳተፉ ተማሪዎች የሚወሰድ የእርምጃ ዓይነት፡- ፈተናን ከተቀመጠበት ቦታ/ክፍል የሠረቀ፣ ያሠረቀ፣ ያሠራጨና የተባበረ ወይም ለሌላ ተማሪ የተፈተነ፣ ሌላ ተማሪ እንዲፈተንለት የፈቀደ ወይም የፈተና መልስ ካልነገርከኝ/ካልሰጠኸኝ በማለት በፈተና አዳራሽ ከተፈታኝ ተማሪ የመልስ ወረቀት የነጠቀ፣ ለመንጠቅ የሞከረ፣ በፈተና አዳራሽ

ውስጥ/በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እና ከትምህርት ቤት ውጭ ያስፈራራ፣ የዛተ፣ ጫና የፈጠረ፣ የፈተና ሥርዓት ያወከ ተማሪ የተፈተነው የፈተናው ውጤት ተሠርዞ ለሁለት ዓመት ከትምህርት ገበታው ይታገድና በቀጥታ በመደበኛ ፍርድ ቤት በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ተወካይ አማካይነት ክስ እንዲመሰረት ይደረጋል፡፡

9.2.6. **ከትምህርት ገበታ የሚቀሩ ተማሪዎችን በተመለከተ**

አንድ ተማሪ ያለበቂ ምክንያት በአንድ መንፈቀ- ዓመት ከትምህርት ቤት በተከታታይ ለ12 (ለአሥራ ሁለት) የትምህርት ቀናት ወይም አቆራርጦ ለ15 (ለአሥራ አምስት) የትምህርት ቀናት ከቀረ ከትምህርት ቤቱ ለአንድ የትምህርት አመት እንዲሰናበትና በዚያው የትምህርት ዘመን ሌላ ትምህርት ቤት ሄዶ እንዳይማር ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የዲሲፕሊን ክስ የሚመለከቱ አደረጃጀቶች፣ ተግባርና ኃላፊነት እና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

### አንቀጽ 10፣ የዲሲፕሊን ክስ የሚመለከቱ አደረጃጀቶች

10.1 **የወረዳው የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ (ወትሥቦ) የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት**

10.1.1 የወረዳው/የከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ ………………………………………. ሰብሳቢ

10.1.2 የወረዳው/ የከተማው ትም/ት ጽህፈት ቤት የመምህራንና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቡድን መሪ/ ባለሙያ ………………………… ጸሐፊ

10.1.3 የወረዳው/የከተማው መምህራን ማህበር ተወካይ (2) አንዷ ሴት ……………………….… አባል

10.1.4 ተከሳሽ የሚገኝበት የቀበሌ የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ ሰብሳቢ (1) ……………………………………………..……….. አባል

10.1.5 የሴቶች ማህበር ተወካይ (1) ............................................... አባል

10.1.6 የወጣቶች ማህበር ተወካይ (1) ………………………..……... አባል

የኮሚቴዉ አባላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ነዉ፡፡

## 10.2 የቀበሌ የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት

10.2.1 የቀበሌው አስተዳዳሪ -----------------------------------------ሰብሳቢ

10.2.2 በቀበሌው ሁለት እና ከዚያም በላይ ትምህርት ቤቶች ካሉ በትምህርት ቤቶች ርዕሣነ መምህራን የሚመረጥ ርዕሠ መምህር---------- ፀሐፊ፣

10.2.3 ሌሎች በቀበሌው ያሉት ትምህርት ቤቶች ርዕሣነ መምህራን---አባል

10.2.4 የሴቶች ማህበር ተወካይ (1) ............................................... አባል

10.2.5 የወጣቶች ማህበር ተወካይ (1) ……....................................... አባል

10.2.6 የት/ቤቱ ወይም የት/ቤቶች *(በቀበሌው ሁለትና ከዚያም በላይት/ቤቶች ካሉ)* ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት ሰብሳቢ እና ሴት አባል በድምሩ (2)------------------------------------------------------ አባል

10.2.7 በቀበሌ ካሉት ትም/ቤቶች የመሠረታዊ መምህራን ማህበራት ተወካዮች (ከየትም/ቤቱ አንዳንድ) --------------------------------- አባል

የዚህ ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ነዉ፡፡

## 10.3 የትምህርት ቤት የዲሲፒሊን ኮሚቴ አባላት

በክልሉ በሚገኙ ቅድመ-አንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚቋቋም አቤቱታ አጣሪና የውሳኔ ሀሳብ አቅራቢ ኮሚቴ ነው፡፡

የኮሚቴ አባላትም የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ሲሆን ተጠሪነቱ ለትምህርት ቤቱ ርዕሠ መምህር ነው፡፡ ርዕሠ መምህሩ እንዳስፈላጊነቱ የኮሚቴ አባላት በሚጓደሉበት ወቅት የማሟላትና ኃላፊነታቸውን ባግባቡ ያልተወጡት ካሉ በኮሚቴው ሲረጋገጥ ሊሻር ወይም ሊለውጥ ይችላል፡፡የትምህርት ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት፡-

10.3.1 በትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ምክትል ርዕሠ-መምህር(1)--- ሰብሳቢ

10.3.2 የትምህርት ቤቱ የመምህራንና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ባለሙያ (1) …………………………………… ፀሐፊ

10.3.3 ሁለት ምክትል ርዕሣነ መምህራን (የአስተዳደርና የአካዳሚክ) ባሉባቸው ትምህርት ቤቶች አካዳሚክ ምክትል ርዕሠ መምህሩ (1) ---- አባል

10.3.4 በቀበሌ የትምህርትና ስልጠና አመራር ቦርድ በአባልነት ያልተካተቱ የትምህርት ቤት የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት አባል (በድምሩ 2) ------------------------------------------------------ አባል

10.3.5 የትምህርት ቤቱ የመሠረታዊ መምህራን ማህበር ተወካይ (2) አንዱ ሴት…………………………………………………..አባል

10.3.6 የተማሪዎች መማክርት ተወካይ (1) ……………………………… አባል

በዚሁ አንቀጽ ተራ ቁጥር 10.3.1 እና 10.3.2 የተጠቀሱት በማይገኙበት እና ባልተመደቡበት ወቅት ከፈረቃው ዩኒት አስተባባሪና ከትምህርት ክፍል ተጠሪ በቅደም ተከተል መሠረት በርዕሠ መምህሩ ይወከላል፡፡

## አንቀጽ 11፣ የዲሲፕሊን ክስ የሚመለከቱ አደረጃጀቶች ተግባርና ኃላፊነት

### 11.1 የክፍል ኃላፊ መምህር ተግባርና ኃላፊነት

11.1.1. በሰንደቅ ዓላማ አከባበር የክፍሉን ተማሪዎች ማስተባበር፤

11.1.2.የክፍሉን ተማሪዎች ውጤትና ዲሲፕሊን በተመለከተ ከወላጆች ጋር መመካከር፤

11.1.3 .ኃላፊ በሆነበት ክፍል ለተማሪዎች ከ2 ቀን ያልበለጠ ፈቃድ መስጠት፤

11.1.4 በትምህርት ወቅት የሚያረፍዱ ተማሪዎችን በመለየት ምክር መስጠት፣ መሻሻሉንም መከታተል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለትምህርት ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፤

11.1.5 ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ ከማንኛውም ዓይነት ጥቃት ጥበቃ የሚደረግላቸውን ስልት መቀየስና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ማድረግ፣

11.1.6 በክፍሉ በሥነ-ምግባራቸው አርአያ የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት የሳምንቱ የሥነ-ምግባር ኮከቦች በማለት በክፍሉ በር ላይ እንዲለጠፍ ማድረግ፣ እንዲሁም ጥሩ ሥነ-ምግባር ያላቸውንና አርዓያ የሆኑ ተማሪዎች በምርጦች መዝገብ እንዲመዘገቡ ማድረግ፣

11.1.7 ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ተማሪዎች ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት የርምጃ ውሣኔ መስጠት፣

11.1.8 ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ተማሪዎች የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ክስ ርምጃ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለፈረቃ/ለዩኒት አስተባባሪ መምህር ማቅረብ፤

11.1.9 የተከናወኑ ሥራዎች መረጃ እና ማስረጃ በአግባቡ አጠናቅሮ መያዝ፣ በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማቅረብ፣ ማሳየት፣ መስጠት፣

## 11.2 የፈረቃ/የዩኒት አስተባባሪ መምህር ተግባርና ኃላፊነት

11.2.2 የሥነ-ምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ከችግሮቻቸው እንዲላቀቁ በእቅድ የሚመራ ተከታታይ የሆነ ግንዛቤ መፍጠር፣

11.2.3 የሥነ-ምግባር ደንቡን የሚጥሱ ተማሪዎችን በመምከር ማስተካከል፤ በምክር የማይመለሱትን በመለየት ውሣኔ መስጠት፣ በጥቁር መዝገብ መመዝገብ ያለባቸውን ተማሪዎች ወላጆች በተገኙበት ከርዕሠ መምህሩ ጋር በመሆን ስማቸውን ማስፈርና መከታተል፣ እንዲሁም በሥነ-ምግባር አርዓያ የሆኑ የፈረቃው ተማሪዎች በምርጦች መዝገብ እንዲመዘገቡ ማድረግ፣

11.2.4 የሥነ-ምግባር መከታተያ መዝገብ በማዘጋጀት ተማሪዎች ጥሩ ሥነ-ምግባር ያላቸው እንዲሆኑ የማድረግ፣

11.2.5 ከ1-4ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ከክፍል ኃላፊ የሚቀርበውን የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የእርምጃ ውሳኔ ሃሳብ በመመርመር ውሳኔ መስጠት፤

11.2.6 ከ5-8ኛ ክፍል ተማሪዎች ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ ላይ የእርምጃ ውሳኔ መስጠት፣

11.2.7 ከ5-8ኛ ክፍል ተማሪዎች የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የእርምጃ ውሳኔ ሃሳብ ለትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ፤

## 11.3 የትምህርት ቤቱ ርዕሠ-መምህር ተግባርና ኃላፊነት

ርዕሠ መምህሩ ተጠሪነቱ ለወረዳው የትምህርት ጽህፈት ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖሩታል፡፡

11.3.1 ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር እንዲታነጹ በሚኒ ሚዲያና በሌሎች መልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ የማስጨበጫ ሥራ መስራት፣

11.3.2 የሥነ-ምግባር መመሪያውን ለተማሪዎች፣ ለመምህራን፣ ሠራተኞችና ለወላጆች በተከታታይነት የማስተዋወቅና ተግባራዊነቱን የመከታተል፣

11.3.3 በስም ጠሪ መምህራን አማካይነት የትምህርት ቤቱን የመተዳደሪያ ደንብ መነሻ በማድረግ የክፍል መተዳደሪያ ደንብ እንዲዘጋጅ ማድረግና ተግባራዊነቱን መከታተል፣

11.3.4. የተማሪዎች የሥነ-ምግባር መከታተያ መዝገብ በማዘጋጀት ለስም ጠሪ መምህራን መስጠትና አፈጻጸሙን የመገምገም እንዲሁም በሥነ-ምግባር አርዓያ የሆኑ ተማሪዎች በምርጦች መዝገብ እንዲሁም የስነ-ሥርዓት ግድፈት የሚያሳዩ ተማሪዎችን በሥነ-ምግባር ግድፈት መከታተያ መዝገብ እንዲመዘገቡ ማድረግ፣

11.3.5. በትምህርት ቤት ደረጃ የሚቋቋሙ በተለይ የሥነ-ምግባር ክበብና ሌሎችም ክበባት በሥነ-ምግባር መተዳደሪያ ደንብ ዙሪያ በተከታታይነት ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፣

11.3.6. በትምህርታቸውና በሥነ-ምግባራቸው ልቀው የተገኙ ተማሪዎችን ማበረታታት፣ መሸለም፣

11.3.7.ተማሪዎች ችግር ሲያጋጥማቸዉ ሪፖርት የሚያደርጉበትን ሥርዓት መዘርጋት፣

11.3.8. ተማሪዎች ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር መሥራት፣

11.3.9. በሥነ-ምግባራቸው ከ1ኛ-3ኛ የወጡ ተማሪዎችን የወሩ የሥነ-ምግባር ኮከቦች ተብለው በትምህርት ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ እንዲለጠፍ ማድረግ፣

11.3.10 . ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ከትምህርት ቤት የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚቀርበውን የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የእርምጃ ውሳኔ ሃሳቦች በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው ያሣውቃል፣

11.3.11 . የተከናወኑ ሥራዎችን መረጃ እና ማስረጃ በአግባቡ አጠናቅሮ መመዝገብ፣ መያዝና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማቅረብ፣ ማሳየት፣ መስጠት፣

## 11.4. የትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

የትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

11.4.1. ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር እንዲታነጹ ማድረግ፤

11.4.2. የሥነ-ምግባር መመሪያውን የሚጥሱ ተማሪዎችን ደረጃውን የጠበቀ እርምጃ መውሰድ፣ ማስወሰድ፣

11.4.3 .ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ከፈረቃ/ከዩኒት አስተባባሪ የሚቀርበውን የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ክስ እርምጃ ውሳኔ ሃሳብ በመመርመር ውሳኔ መስጠት፤

11.4.4 . ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ ላይ እርምጃ መዉሰድ፣

11.4.5 . ከ9-12ኛ ክፍል ተማሪዎች የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ክስ የእርምጃ ውሳኔ ሃሳብ ለርዕሠ-መምህር ማቅረብ፤

11.4.6 . ከ1ኛ-4ኛ የትምህርት እርከን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተሰጣቸው ከባድ የዲስፕሊን እርምጃ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ ወይም ቅሬታ በመቀበል ውሳኔ መስጠት፣

11.4.7 . ከ5ኛ-8ኛ የትምህርት እርከን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተሰጣቸው ቀላል የዲስፕሊን እርምጃ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ ወይም ቅሬታ በመቀበል ውሳኔ መስጠት፣

13.4.1 . መመሪያውን ማስተዋወቅና የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን መሥራት፤

13.4.2 . በቀረቡት አቤቱታዎች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከመቅረቡ በፊት ጥፋቱ ለተቋሙና ለከሳሹ ከባድና አስጊ ሆኖ ሲገኝ ጥፋቱ እንዲቆም ጊዜያዊ ትዕዛዝ መስጠት፤

13.4.3 . በኮሚቴ አባልነቱ ያወቃቸውን ማንኛውንም ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮችን በሚስጥር መጠበቅ፡

13.4.4 . የሚቀርቡ አቤቱታዎች ሲመረመር አቤቱታ አቅራቢን፣ አቤቱታ የቀረበበትን ወይም ምስክሮችን የመጥራትና የመስማት፣ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች (የጽሑፍና ሌሎች ማስረጃዎች) እንዲቀርቡለት የማዘዝ፣ ሰነዱ ባለበት ቦታ ሄዶ የማየትና ሌሎች ለምርመራ ተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ፤

13.4.5 . ኮሚቴው የአቤቱታ ማመልከቻ ቅፃቅፆችን ማዘጋጀት፤

13.4.6 . በቀረቡት አቤቱታዎች እንደየጥፋቱ ቅለትና ክብደት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሣኔ መስጠት፣ የውሳኔ ሀሳብ በአብላጫ ድምጽ ይወሰናል፡፡ድምጽ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወሳኝ ድምጽ ይሆናል፡፡

13.4.7 . ኮሚቴው በመደበኛነት በየወሩ አንድ ጊዜ በተማሪዎች ሥነ-ምግባር ለውጥ ዙሪያ በመወያየት ወቅታዊ ሂደቱን ለርዕሠ መምህሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

13.4.8 . ዲስፕሊን ኮሚቴው የተከናወኑ ሥራዎች መረጃና ማስረጃ አጠናቅሮ መመዝገብ፣ መያዝና በርዕሠ-መምህሩ ሲጠየቅ ማቅረብ፣ ማሳየት፣ መስጠት፣

## 11.5 የቀበሌ ትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

የዚህ አመራር ቦርድ አባላት የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

11.5.1. ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የማድረግ፣

11.5.2. ተማሪዎች በመልካም ስነ-ምግባር እንዲታነጹ ማድረግ፤

11.5.3. በቀበሌ ደረጃ በሚካሄዱ ስብሰባዎች ላይ በተማሪዎች ሥነ-ምግባር ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንዲሠራ ማድረግ፣

11.5.4. ከ5ኛ-8ኛ የትምህርት እርከን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተወሰደባቸው ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ክስ ርምጃ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ ወይም ቅሬታ በመቀበል ውሳኔ መስጠት፣

11.5.5. ከ9ኛ-12ኛ የትምህርት እርከን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተሰጣቸው ቀላል ጥፋት ክስ ርምጃ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ ወይም ቅሬታ በመቀበል ውሳኔ መስጠት፣

11.5.6. የተከናወኑ ሥራዎችን መረጃ እና ማስረጃ በአግባቡ አጠናቅሮ መመዝገብ፣ መያዝና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማቅረብ፣ ማሳየት፣ መስጠት፣

## 11.6. የወረዳ ትምህርትና ስልጠና አመራር ቦርድ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

### 11.6.1. የወረዳው የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አባላት

11.6.1.1. የወረዳው/ የከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ ወይም ምክትል ኃላፊ በሌለበት የከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት በኃላፊ የሚወከል የማኔጅመንት አባል ወይም የከተማው አስተዳደር ትምህርት ዩኒት አስተባባሪ (1)…….ሰብሳቢ

11.6.1.2. የወረዳው/ የከተማው ትምህርት ጽህፈት ቤት ወይም የከተማ ትምህርት ዩኒት የመምህራንና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቡድን መሪ (1)……. ጸሐፊ

11.6.1.3. የወረዳው/ የከተማው አስተዳደር መምህራን ማህበር ተወካይ (2) አንዷ ሴት ……አባል

11.6.1.4. ተከሳሽ የሚገኝበት የቀበሌ የትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ ሰብሳቢ (1)….አባል

11.6.1.5. የሴቶች ማህበር ተወካይ (1)............አባል

11.6.1.6. የወጣቶች ማህበር ተወካይ (1)……. አባል

### 11.6.2. የዲሲፕሊን ኮሚቴዉ ተግባርና ኃላፊነት

11.6.2.1. ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ማለትም ከፖሊስ፣ ከቀበሌ/ከተማ አስተዳደር፣...ወዘተ ጋር በመቀናጀት ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ የተማሪዎች ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን የማድረግ፣

11.6.2.2. ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር እንዲታነጹ ማድረግ፤

11.6.2.3. ከ9ኛ-12ኛ የትምህርት እርከን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በተሰጣቸው ከባድ ጥፋት ክስ እርምጃ ላይ የሚቀርበውን ይግባኝ ወይም ቅሬታ በመቀበል ውሳኔ መስጠት፣

**11.6.2.4.** የተከናወኑ ሥራዎች መረጃ እና ማስረጃ በአግባቡ አጠናቅሮ መመዝገብ፣ መያዝና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማቅረብ፣ማሳየት፣መስጠት፣

## አንቀጽ 12. ክስ አመሰራረት

12.1 አጥፊ ተማሪ የክፍል ደረጃው ከ1ኛ እስከ 4ኛ በሚሆንበት ጊዜ ተበዳይ አካል ወይም የትምህርት ቤቱ ተወካይ አጥፊውን ተማሪ ለይቶ ጥፋቱን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን (ማስረጃዎቹ የጽሑፍ ወይም የሰው ምስክሮች ሊሆኑ ይችላሉ)፣ ዝርዝር ጥፋቱን፣ የተከሳሽ ሙሉ ስም፣ የክፍል ደረጃ እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመበት ቦታና ጊዜ ባጭሩ በመግለጽ በቃልም ሆነ በጽሑፍ ክሱን ለክፍል ኃላፊ መምህር ያቀርባል፡፡

12.2 አጥፊ ተማሪ የክፍል ደረጃው ከ5ኛ እስከ 8ኛ በሚሆንበት ጊዜ ተበዳይ አካል ወይም በክፍል ኃላፊ መምህር ወይም በትምህርት ቤቱ ተወካይ አጥፊውን ተማሪ ለይቶ ጥፋቱን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን (ማስረጃዎቹ የጽሑፍ ወይም የሰው ምስክሮች ሊሆኑ ይችላሉ)፣ ዝርዝር ጥፋቱን፣ የተከሳሽ ሙሉ ስም፣ የክፍል ደረጃ እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመበት ቦታና ጊዜ ባጭሩ በመግለጽ ክሱን ለፈረቃው መሪ ወይም ለዩኒት አስተባባሪ ያቀርባል፡፡

12.3 .አጥፊ ተማሪ የክፍል ደረጃው ከ9ኛ እስከ 12ኛ በሚሆንበት ጊዜ ተበዳይ አካል ወይም በክፍል ኃላፊ መምህር ወይም በትምህርት ቤቱ ተወካይ አጥፊውን ተማሪ ለይቶ ጥፋቱን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን (ማስረጃዎቹ የጽሑፍ ወይም የሰው ምስክሮች ሊሆኑ ይችላሉ)፣ ዝርዝር ጥፋቱን፣ የተከሳሽ ሙሉ ስም፣ የክፍል ደረጃ እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመበት ቦታና ጊዜ ባጭሩ በመግለጽ ክሱን ለትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 13. የምርመራና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

### 13.1 .የቀላል ክስ ምርመራና እርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ

ሀ) ክሱን የሚመለከተው ክፍል/አካል ከሳሽና ተከሳሽን በጋራ በማነጋገር፣ ማስረጃዎችን (የጽሑፍና የሰው)በማጣራት በ1/አንድ/ ቀን ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ለ) ክሱን ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠው ክፍል/አካል የጥፋቱን ዓይነትና የተሰጠውን ውሳኔ በጽሑፍ ለተከሳሽ ተማሪ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ የከባድ የውሳኔ ሀሳብ ለሚያጸድቀውም ክፍል/አካል በግልባጭ ያሳውቃል፡፡

### 13.2 . ከባድ የስነ-ምግባር ጥፋት ክስ ምርመራና ውሳኔ አሰጣጥ

ሀ) ክሱን ተመልካች ክፍል/አካል ተከሳሽ በ5/አምስት/ የትምህርት ቀናት መልስ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ ተከሳሽ የክሱን ምላሽ ካቀረበ በኋላ ከሳሽና ተከሳሽን በማከራከር፣ ምስክሮቻቸውን በመስማትና ማስረጃዎችን በመመርመር ተከሳሽ ጥፋተኛ መሆኑንና አለመሆኑን /ክሱን/ ያጣራል፡፡

ለ) ከላይ በ(ሀ) ላይ እንደተጠቀሰው ተከሳሽ ተማሪ ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ግን ክሱን የሚመለከተው ክፍል/አካል እርምጃዉን/ቅጣቱን ለማክበድ ወይም ለማቅለል እንዲያስችለው የተማሪዉን አጠቃላይ ሁኔታ ማለትም ከክሱ በፊት የነበረውን መልካም ስነ-ምግባር፣ የቀድሞ የዲሲፕሊን ጥፋት ሪከርድ በማገናዘብ የውሳኔ ሀሳብ/አስተያየት የከባድ የውሳኔ ሀሳብ ለሚያጸድቀውም ክፍል/አካል ያቀርባል፡፡

መ) ከላይ በ(ለ) ላይ በተጠቀሰው መሰረት የከባድ የውሳኔ ሀሳብ/አስተያየት ለሚመለከተው ክፍል/አካል ሲቀርብ ተመልካቹ ክፍል/አካል ውሳኔውን በበቂ ማስረጃዎች ስለመመስረቱ፣ ለክሱ/ለጥፋቱ ተመጣጣኝ ቅጣት የውሳኔ ሀሳብና የተማሪው የመከላከያ መብት የተጠበቀለት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ውሳኔውን ማጽደቅ ወይም ክሱ እንደገና እንዲታይ ወይም የውሳኔ ሀሳብ/አስተያየት እንዲሻሻል ማድረግ ይችላል፡፡ በዚህም ክፍል የጸደቀውን ውሳኔ ክሱን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ላቀረበው ክፍል/አካል ለተከሳሽ ተማሪ በጽሑፍ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 14. የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

### 14.1 . ከ1ኛ-6ኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ

ሀ) ቀላል የሥነ-ምግባር ጥፋት ከሆነ ከቀላል እርምጃ ዓይነቶች አንዱ እርምጃ በክፍል ኃላፊው መምህር ሲወሰን በእርምጃ አወሳሰድ ዙሪያ ተማሪው ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለፈረቃው ዩኒት/ፈረቃ አስተባባሪ በማቅረብ ውሳኔ በአንድ ቀን ውስጥ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

ለ) ከባድ የሥነ-ምግባር ጥፋት ከሆነ ግን በ5 የትምህርት ቀናት ውስጥ ከከባድ እርምጃ ዓይነቶች ውስጥ አንዱ እርምጃ በፈረቃው ዩኒት አስተባባሪ መምህር እንዲወሰን/እንዲጸድቅ የክፍል ኃላፊ መምህሩ የውሳኔ ሀሳብን ከማስረጃዎች ጋር በማያያዝ ያቀርባል፡፡ሲጸድቅም በርምጃ አወሳሰዱ ዙሪያ ተማሪው ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለትምህርት ቤቱ ዲሲፕሊን ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ በአንድ ቀን ውስጥ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

### 14.2 ከ7ኛ-8ኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ

ተማሪው ቀላልም ሆነ ከባድ የሥነ-ምግባር ጥፋት ከፈጸመ ክስ ለፈረቃው የፈረቃ/የዩኒት አስተባባሪ መምህር ይቀርብና ሂደቱን በማጣራት፡-

ሀ) ቀላል የሥነ-ምግባር ጥፋት ከሆነ በአንድ ቀን ውስጥ ከቀላል እርምጃ ዓይነቶች አንዱ እርምጃ በፈረቃው የፈረቃ/የዩኒት አስተባባሪ መምህር ሲወሰን በእርምጃ አወሳሰዱ ዙሪያ ተማሪው ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለትምህርት ቤቱ ዲሲፕሊን ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ በአንድ ቀን ውስጥ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

ለ) ከባድ የሥነ-ምግባር ጥፋት ከሆነ ግን በ5 የትምህርት ቀናት ውስጥ ከከባድ እርምጃ ዓይነቶች ውስጥ አንዱ እርምጃ በትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲወሰን/እንዲጸድቅ በፈረቃው የፈረቃ/የዩኒት አስተባባሪ መምህሩ የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ ሲፀድቅ ተማሪው ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለቀበሌ የትምህርትና ስልጠና አመራር ቦርድ (ቀትሥቦ) በማቅረብ ውሳኔ በሁለት ቀናት ውስጥ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

14.3 **ከ9ኛ-12ኛ ክፍል የትምህርት ደረጃ**

ተማሪው ቀላልም ሆነ ከባድ የሥነ-ምግባር ጥፋት ከፈጸመ ክስ ለትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ይቀርብና ሂደቱን በማጣራት፡-

ሀ) ቀላል የሥነ-ምግባር ጥፋት ከሆነ በአንድ ቀን ውስጥ ከቀላል ርምጃ ዓይነቶች አንዱ እርምጃ በትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሲወሰን በእርምጃ ዙሪያ ተማሪው ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለቀበሌ የትምህርትና ስልጠና አመራር ቦርድ በማቅረብ ውሳኔ በአንድ ቀን ውስጥ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

ለ) ከባድ የሥነ-ምግባር ጥፋት ከሆነ ግን በ5 የትምህርት ቀናት ውስጥ ከከባድ እርምጃ ዓይነቶች ውስጥ አንዱ እርምጃ በትምህርት ቤቱ ርዕሠ-መምህር እንዲወሰን/እንዲጸድቅ በትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ሲጸድቅ ተማሪው ቅሬታ ካለው ቅሬታውን ለወረዳው የትምህርትና ስልጠና አመራር ቦርድ በማቅረብ ውሳኔ በሶስት ቀን ውስጥ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 15፣ የከባድ ዲስፕሊን እርምጃ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ስለሚተላለፍበት ሁኔታ

ሀ) በከባድ የዲስፕሊን እርምጃ ተቀጥቶ ከትምህርት ቤት የታገደ ተማሪ ቅጣቱን ወይም የይርጋ ጊዜውን ሳይጨርስ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ያለመሸኛ ሂዶ ተመዝግቦ እየተማረ መሆኑ ከታወቀ የዲስፕሊን ውሳኔዎች ለትምህርት ቤቱ እንዲደርስ በማድረግ እንዳይማር ይደረጋል፡፡

ለ) ያለመሸኛ ተማሪውን መዝግቦ በማስተማሩ ድርጊቱን የፈጸመው ማንኛውም መምህር ወይም የትምህርት ቤት አመራር ወይም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችና ተወካዮች አግባብነት ባለዉ የዲሲፕሊን አፈፃጸም መመሪያ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 16. ክስ የሚመሰረትበት የጊዜ ገደብ /የይርጋ ጊዜ/

ሀ) ቀላል የዲሲፕሊን እርምጃ የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ ተማሪ የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር በጥፋቱ ካልተቀጣ በቀጣይ ተጠያቂ አይሆንም፣

ለ) ከባድ የዲሲፕሊን እርምጃ የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ ተማሪ የፈፀመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጥፋቱ ካልተከሰሰ በዲሲፕሊን ጥሰት ተጠያቂ  አይሆንም፡፡

ሐ) ከባድ ዲስፕሊን ክሶችን እንዲያይ በዚህ መመሪያ ውስጥ ሥልጣን የተሰጠው አካል የይርጋ ጊዜ በማለፉ ምክንያት ተማሪው በጥፋቱ አለመከሰሱን ወይም አለመቀጣቱን አውቆ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ያላሳወቀ አካል በፍርድ ቤቱ በተባባሪ ጥፋተኛነት ይጠየቃል፡፡ አግባብነት ባለዉ የዲሲፕሊን አፈፃጸም መመሪያ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ17. ከባድ እርምጃ ተወስኖበት ከትምህርት ቤት የታገደ ተማሪ ተመልሶ መማር/መግባት ስለሚችልበት ሁኔታ

ሀ)ማንኛውም ተማሪ በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ከባድ እርምጃ ተወስኖበት ከትምህርት ቤት ከታገደ በአንቀጽ 14 (ለ) እንደተመለከተው የመቆያ ጊዜውን ከጨረሰ ከሚኖርበት ቀበሌ የሥነ-ምግባር ለውጥ ማምጣቱን እና እርምጃ ከተወሰደበት የሥነ-ምግባር ችግር የተላቀቀ ስለመሆኑ ለወረዳው/ለከተማው አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ በማቅረብ በማኔጅመንት ሲወሰን በውሳኔዉ መሠረት በቀድሞ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ እንዲማር ይደረጋል፡፡

ለ) ተማሪው ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ተዛውሮ ለመማር ሲፈልግ ግን በቀድሞ ትምህርት ቤት እስከ 6/ስድስት/ ወር ማለትም እስከ አንደኛ መንፈቀ-ዓመት ትምህርት መጨረሻ ድረስ ትምህርቱን ሲከታተል/ሲማር ቆይቶ የሥነ-ምግባር መሻሻል አሳይቶ ከሆነ ወይም ቀደም ሲል ከነበሩ ጥፋቶች መታረሙን የቀድሞው ትምህርት ቤት ከገመገመ በኋላ መሸኛ በመስጠት መሸኘት ይቻላል፡፡ ነገር ግን  የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ አካባቢ በሚቀይሩበት ወቅት

ወይም ሌላ አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም ተማሪውን መሸኛ ተሰጥቶት በሌላ ትምህርት ቤት ትምህርቱን እንዲከታተል/ እንዲማር ማድረግ ይቻላል፡፡

ሐ) የተወሰነበትን ጊዜ ሳያጠናቅቅ በወላጅ/አሳዳጊ ዝውውር ወይም ሌላ አስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት ወደ ሌላ አካባቢ የሚዛወር ተማሪ የውሣኔው ኮፒ ከመሸኛው ጋር ተያይዞ በፖስታ ታሽጎ ለአዲሱ ትምህርት ቤት ይላካል፣ ትምህርት ቤቱም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 18. የዲስፕሊን ክስ ውሣኔ እና የመሻር ሥልጣን

ሀ) በትምህርት ቤት የሚታይ የዲስፕሊን ክስ ማንኛውንም የፍርድ ቤት ውሣኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል በዚህ መመሪያ ላይ የክሱን ሂደት የሚመለከቱ እና የእርምጃ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት ታይቶ ይወሰናል፡፡

ለ) ተማሪው የሚማርበት ትምህርት ቤት ያሳለፈውን ውሣኔ ቀጥሎ ያለ ተቋም የመሻር ሥልጣን የለውም፡፡ ሆኖም በውሣኔዎቹ ቅሬታ ያለው ተማሪ ቅሬታውን በአንቀጽ 11 በተመለከተው የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት መሠረት ማቅረብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 19. ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት አጥፍቶ የተሰወረ ተማሪ በህግ ስለሚጠየቅበት ሁኔታ

ከላይ በአንቀጽ 13 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተከሳሽ ከነበረበት ትምህርት ቤት መሸኛ ሳይዝ በሌላ ትምህርት ቤት ተመዝግቦ በመማር ላይ መገኘቱ ከታወቀ ውሳኔው ለትምህርት ቤቱ ይተላለፋል፡፡

ሆኖም ተከሳሽ ከፍተኛ የሆነ የመንግስት ንብረትና ሀብት በማጥፋት ተሰውሮ ወደ ትምህርት ቤት ሳይመለስ የቀረና በማንኛውም ጊዜ ተከሳሽ በሀገር ውስጥ እንዳለ አድራሻው ሲታወቅ የክስ ውሳኔውን ያስተላለፈው ክፍል አግባብነት ባለው ሕግ እንዲጠየቅ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ለወረዳ/ ለከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ሪፖርት በማድረግ በአካባቢ በሚገኙ ፖሊስ እና መደበኛ ፍርድ ቤት እንዲጠየቅ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች ጭምር ለድርጊቱ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ለጠፋውም

የመንግስት ሀብትና ንብረት ጉዳት/ጉድለት የተማሪው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ማካካሻ እንዲተካ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 20. የተጠያቂነት ሁኔታ**

ይህንን መመሪያ እንዲያስፈጽም ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም ክፍል ወይም አካል በተቀመጠው የአሠራር ሥርዓት መሠረት ሳይፈጽም ከተገኘ አግባብ ባለው የዲሲፕሊን አፈፃጸም መመሪያ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 21. የመመሪያው ተፈፃሚነት፣ የሚሻሻልበትና የሚፀናበት ሁኔታ**

ሀ) መመሪያውን የማሻሻል አስፈላጊነት ሲታመን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ የሚሻሻል ይሆናል፡፡

ለ) ይህ መመሪያ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ሥነ-ሥርዓት በሚያጎድሉ ተማሪዎች ላይ የሚወሰዱ ውሳኔዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውም ሆነ ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች በዚህ መመሪያ የተተኩ ስለሆነ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

ሐ) ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመረ የተማሪ የሥነ-ምግባር ጥፋት ክስ ካለ ቀደም ሲል ተፈፃሚ ይሆን በነበረው አፈፃጸም መሠረት ውሳኔ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

መ) ይህ መመሪያ ከ----------------------- ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አንተነህ ፈቃዱ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር፣

የማህበራዊ ክለስተር አስተባባሪና የትምህርት ቢሮ ኃላፊ

## <u>አባሪ አንድ፣ የማጣቀሻ መጻሕፍት</u>


1. የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት ገዥ መመሪያ (Blue Print)፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1999 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

2. የትምህርት አመራር፣ አደረጃጀት፣ የሕብረተሰብ ተሣትፎና የፋይናንስ መመሪያ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1994 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

3. የተማሪዎች የሥነ-ምግባር መተዳደሪያ ደንብ፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ፣ 2007 ዓ.ም፣ ባህር ዳር

4. አዎንታዊ የሕፃናት ሥነ-ምግባር አጠባበቅ ማኑዋል፡፡ የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ከSave the Children Sweden እና ከአንፐካን ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው፣ ዓ.ም. ያልተጠቀሰ፣ አዲስ አበባ

5. በትምህርት ቤቶች የሚፈጸም ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከል የወጣ መመሪያ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 2007 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

6. የትምህርት ቤቶች የውስጥ አመራርና አስተዳደር መመሪያ (ጥራዝ አንድ)፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1980 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

7. የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 2001 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

8. በቀድሞ ደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ትምህርት ሴክተር የመምህራን፣ የርዕሳነ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የዲስፕሊን አፈፃጸም መመሪያ

9. የሕጻናት ኮንቨንሽን

## አባሪ ሁለት፣ የዲስፐሊን ውሣኔ አሰጣጥና የቅሬታ አቀራረብ

1) ቀላል ዲሲፐሊን

| የትምህርት እርከን | ቀላል የዲስፐሊን ርምጃ የሚያስከትሉ ጥፋቶች | ውሣኔ ሰጪ | ቅሬታ ሰሚ |
|---|---|---|---|
| ቅድመ-መደበኛ | ---- | የክፍል ኃላፊ መምህር | ----- |
| 1ኛ-4ኛ ክፍል | ንዑስ አንቀጽ 8.1.1 እስከ 8.1.10 | የክፍል ኃላፊ መምህር | ዩኒት መሪ ወይም ፈረቃ አስተባባሪ |
| 5ኛ-8ኛ ክፍል | ንዑስ አንቀጽ 8.1.1 እስከ 8.1.10 | ዩኒት መሪ ወይም ፈረቃ አስተባባሪ | የት/ቤቱ ዲሲፐሊን ኮሚቴ |
| 9-12ኛ ክፍል | ንዑስ አንቀጽ 8.1.1 እስከ 8.1.10 | የት/ቤቱ ዲሲፐሊን ኮሚቴ | የቀበሌ ትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ (ቀትሥቦ) |

2) የከባድ ዲሲፐሊን

| የትምህርት እርከን | ከባድ የዲስፐሊን ርምጃ የሚያስከትሉ ጥፋቶች | ውሣኔ ሰጪ | ቅሬታ ሰሚ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ-4ኛ ክፍል | ንዑስ አንቀጽ 8.2.1 እስከ 8.2.28 | ዩኒት መሪ ወይም ፈረቃ አስተባባሪ | የት/ቤቱ ዲሲፐሊን ኮሚቴ |
| 5ኛ-8ኛ ክፍል | ንዑስ አንቀጽ 8.2.1 እስከ 8.2.28 | የት/ቤቱ ዲሲፐሊን ኮሚቴ | የቀበሌ ትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ (ቀትሥቦ) |
| 9-12ኛ ክፍል | ንዑስ አንቀጽ 8.2.1 እስከ 8.2.28 | የውሣኔ ሃሣብ በዲሲፐሊን ኮሚቴ የቀረበለትን አይቶ ርዕሠ-መምህር | የወረዳ ትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ (ወትሥቦ) |